**ሳምንታዊ ዜና (የካቲት 2፣ 2000 ዓ. ም.)**

**ወያኔ በታጣቂ ሃይሎች ፍራቻ ጎንደር ውስጥ ገበሬዎችን መሳሪያ አስፈታ፣ ትግራይ ሰሜን እዝ ውስጥ ያሉ አባላት ለምን የትግራይ ሴት አገባችሁ ተብሎ ወከባ እየደረሰባቸው ነው፣ የወያኔ ደህንነትና ፖሊስ ባለስልጣናት ምስጢራዊ ስብሰባ አደረጉ፣ በአዲስ አበባ ወጣቱና ፖሊስ በየቀኑ ይፋለማሉ፣ ከጂማም የኦነግ አባል ሳይሆኑ አይቀሩም በሚል ጥርጣሬ 5 ወጣቶ ች ተይዘው መሿለኪያ ካምፕ ውስጥ ታስረዋል »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»**

**ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ**

ወያኔ ሕዝቡን ከመጠራጠሩ የተነሳ ለራሳቸው መጠበቂያ በእጃቸው የሚገኘውን መሣሪያ እንዲያስመዘግቡ መደረጉን ከተለያዩ አካባቢዎች የደረሰን ዘገባ ገለፀ።

ከጎንደር የደረሰን ዘገባ እንደሚያስረዳው የወያኔ ቡድን በሕዝቡ ላይ ካለው ከፍተኛ ጥርጣሬ የተነሳ በገጠር ውስጥ ያሉ ታጣቂዎችን የታጠቃችሁትን መሣሪያ አስመዝግቡና ሕጋዊ ማስረጃ ሰጥተናችሁ ትመለሳላችሁ በማለት ምዝገባ መጀመራቸውን ገልጿል።

በተለይም በጎንደር ውስጥ ታጣቂ የተቃዋሚ ኃይል ይንቀሳቀሳል ተብሎ እየተነገረ ባለበት በዚህ ወቅት የወያኔው ቡድን ባደረበት ከፍተኛ ስጋት የተነሳ በጎንደር ክፍለ ሀገር ውስጥ ያሉ ታጣቂዎች በሙሉ እንዲመዘገቡ መመሪያ ካስተላለፈ ቢቆይም ታጣቂው ሕዝብ አሻፈረኝ በማለቱ በዘዴ አሁን ሰሞኑን አዲስ ስልት በመቀየስ ምዝገባ መጀመሩን ይኸው የደረሰን ዘገባ አስድቷል።

በዚሁ በተደረገው ምዝገባ እቤት ውስጥ ለችግር ጊዜ ተብሎ የተቀመጠ መሣሪያ እንኳዋን ቢኖር ህጋዊ ፈቃድ እንሰጣችኋለን በማለት በማታለል የመዘገዋቸው ሲሆን የጥይት ብዛቱንም ጭምር ምዝገባ ያከናወኑ መሆኑን ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልፆ ወያኔ ባደረበት ከፍተኛ ስጋት የተነሳ የገጠሩ ሕዝብ እራሱን የሚጠብቅበትን መሣሪያ «ሕጋዊ ለማድረግ» በሚል ምዝገባ ያካሄዱ ከመሆኑም ባሻገር በቅርብ ጊዜ ውስጥ ደግሞ መሣሪያውን የማስፈታት ስራ ሊያከናውን ይችላል ተብሎ ሥጋት ማሳደሩን ገልጿል።

የወያኔ ቡድን በሕዝብ ላይ በሚፈፅመው ግፍና በደል የተነሳ በየአጋጣሚው ሁሉ ከመሀል ሀገርም ሆነ ከየትኛውም የሐገሪቷ ክፍል እየተሰደዱ በየጠረፉ ካሉ ተቃዋሚዎች ጋር እየተቀላቀሉ የወያኔን ቡድን ፍዳ ለማብላት እየተዘጋጁ መሆኑ እየተነገረ ሲሆን፣ በሰሜን ኢትዮጵያ በተለይ በጎንደር ውስጥም አንድ የተጠናከረ የተቃዋሚ ታጣቂ ኃይል መኖሩን የወያኔው ቡድን ጭምር ያመነ ሲሆን አሁንም የጎንደር አርሶ አደር ከዚህ ታጣቂ ቡድን ጋር ይወግናል ብሎ ስጋት ስላደረበት



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ብቻ ከአርሶ አደሩ ላይ መሣሪያ ለመንጠቅ መዘጋጀቱን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ዛሬ በጐንደር ውስጥ የተጀመረው መሣሪያ ምዝገባ ወደ ጐጃምና ሸዋ መዝለቁ አይቀሬ ነው ያሉት አንዳንድ የጐንደር አርሶ አደሮች ከእኛ ትምህርት ወስደው ሁሉም ዘዴ መዘየድ አለበት፡፡ አሁን ወያኔ የተያያዘችው ሁላችንንም ትጥቅ አስፈትታ እንደልቧ ልትነዳን ነው ስለዚህ ሁሉም የሀገሬ ሕዝብ ልብ ሊል ይገባል በማለት ምክር ለግሰዋል፡፡

ወያኔ በእንዲህ ያለ ፍርሀትና ጭንቀት ውስጥ እያለ በሰሜን እዝ ውስጥ ያሉ ወታደሮችን ደግሞ እያስፈራራ እና በጥያቄ እያጣደፋቸው መሆኑን ከመቀሌ የደረሰን ዘገባ ገልጿል፡፡

የአማራና የኦሮሞ ተወላጅ ወታደሮች በትግራይ ውስጥ የትግራይ ልጆችን በትዳር ጓደኝነት ይዘው ትዳር መስርተው የተቀመጡትን ወታደሮች የየክፍለ ጦሩ አዛዥ መኮንኖች እያስጠሯቸው ለምን የአማራ ተወላጅ ሆነህ የትግራይ ሴት ልታገባ ቻልክ? እየተባሉ የቁም ስቃይ እያሳዩዋቸው መሆኑን ይኸው ከመቀሌ የደረሰን ዘገባ ገልጿል፡፡

ከዚህ ቀደም የደርግ ወታደሮች በኤርትራና በትግራይ ውስጥ በነበሩበት ወቅት ፍቅር ከያዛቸው ጋር ትዳር መስርተው ልጆች ወልደው ለትልቅ ደረጃ ደርሰው ያሉ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን አሁን ግን የወያኔ ቡድን በሰሜን ያሰፈረው የጦሩ አባላት የትግራይን ልጅ ሲያገቡ ለምን አገባህ? በማለት በጥያቄ እያጣደፏቸው ከመሆኑም ባሻገር ከጀርባው የያዘከው ተንኮል ወይም ተልእኮ አለህ በማለት ለዘመናት በብሔርና በቋንቋ ሳይለያይ የተዋለደውን ሕዝብ ለመከፋፈል እየተሯሯጡ መሆኑን የደረሰን ዘገባ አስረድቷል፡፡ በዚህም የተነሳ በርካታ ወታደሮች ከደመወዛቸው ሰበብ እየተፈለገባቸው እየተቆረጠ እንደሚገኝ ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል፡፡

ወታደሩን የቁም ስቅል እየሳየ የገጠሩን ታጣቂ መሣሪያውን ለመግፈፍ እየተሯሯጠ ያለው የወያኔ ቡድን ሰሞኑን ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ የገቡትን ኤርትራያውን ደብረማርቆስና አዲስ አበባ እንዲኖሩ ሕጋዊ ፈቃድ ሰጥቶ ከትግራይ ወደየቦታው ያጓጓዛቸው መሆኑ ታወቀ፡፡

ሻዕቢያና የሻዕቢያ ወኪሎች ናቸው በማለት በ1992 ዓ.ም ከመላ ሐገሪቷ ውስጥ ወልደውና ተዋልደው ለዘመናት የኖሩትን ኤርትራያውንን «የአይናቸው ቀለም አላማረንም» በማለት መለስ ዜናዊ እያመናጨቀና እያንገላታ ያባረራቸው ሲሆን ዛሬ ደግሞ በከፍተኛ መስተንግዶ አቀባበል ካደረገላቸው በኋላ እንደገና ወደ ደብረማርቆስ እና አዲስ አበባ ሕጋዊ ፈቃድ ሰጥቶ እንዲኖሩ ማድረጉ ታውቋል፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

አንድ የትግራይ ተወላጅ ነጋዴ እንደገለፁት ከሆነ እነ መለስ ዜናዊ ሕዝቡን ከናቁ ቆይተዋል ዛሬ መላው ዜጐች በኑሮ ወድነት ከመቼውም ጊዜ በላይ እየተቃጠሉ ባሉበት ወቅት ነዳጅ ጨምሮ እያንገበገበን ሲሆን እንደገና ይህም አልበቃ ብሎት የኤርትራን ስደተኞችን አምጥቶ ከሕዝቡ ጋር መቀላቀሉ የራሱን ሽክም ሕዝቡ እንዲሸከም ከማድረጉም በላይ ሕዝቡ ምን ያመጣል የሚል ንቀት መሆኑን በግልፅ ያሳያል ሲሉ በእህልና በንዴት ገልፀዋል።

ሌላው የአዲስ አበባ ነዋሪ እንዳሉት ከሆነ ደግሞ እነመለስ ዜናዊ ጤንነታቸው በእጅጉ ያጠራጥራል ከዚህ ቀደም የአይናቸው ቀለም አላማረንም ብለው ከቤት ንብረታቸው ልጆቻቸውን ትተው፣ ባል ሚስትን፣ ሚስት ባልና ልጆቿን ትታ እንድትሰደድ አደረጉ ዛሬ ደግሞ የሻዕቢያ ተላላኪዎች ናቸው በማለት በመገናኛ ብዙሃን ሲለፍፉ ቆይተው አሁን ደግሞ ሕጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ሰጥተው ከሕዝቡ ጋር መቀላቀላቸው ምን እየሰሩ እንደሆነ የሚያውቁ አይመስለኝም በማለት በንዴት ሲገልፁ ተደምጠዋል።

አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ በትግራይ ውስጥ እንዲኖሩ ያልተደረገው የትግራይ ተወላጆችና የኤርትራ ተወላጆች ከበፊት ጀምሮ የማይዋደዱና የማይግባቡ መሆናቸው ስለሚታወቅ በትግራይ ውስጥ ቢቀመጡ አደጋ ሊደርስባቸው ይችላል? ከሚል ስጋት በመነጨ ወደ ደብረማርቆስ እና አዲስ አበባ እንዲቀመጡ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ሲሉ ያላቸውን አስተያየት ገልፀዋል።

በሌላ በኩል የእነ መለስ ነፍስ አባት የሆኑት አባ ገ/መድህን የሚሊኒየሙ አባት በሚል ቅዳሜ ጥር 24 ቀን 2000 ዓ.ም በስብሰባ ማዕከል ትልቅ ዋንጫ መሸለማቸው ታወቀ።

ከ6 ወር በፊት በራሳቸው አባ ገመድህን መልማይነት 16 አባላት ያሉበት የገንዘብ ሰብሳቢ ኮሚቴ በታዘዘው መሠረት ከየደብሩ የሙዳይ ምፅዋት እየገለጡ ገንዘብ የሰበሰቡ እና ሐመር መኪና ሊገዙ በዝግጅት ላይ የነበሩ ቢሆንም ኮሚቴው በሀሳብ ባለመስማማቱ ለሁለት ተሰንጥቆ አንደኛው ቡድን ሰብሳቢውን ጨምሮ 12 አባላት ያሉት የሽልማቱ ጊዜ ይራዘም ቢሉም 4 አባላት ያሉት ሙሉጌታ አስራት ካሣ ያለበት ቡድን ግን አሁኑኑ ይሁን በማለት የታቀደው መኪና እና ሌሎች ነገሮች ሳይሟሉ የሽልማት አሰጣጡ ስነ ስርዓት ተካሂዷል።

በዚህ ሽልማት ስነ ስርዓት ላይ መለስ ዜናዊ ቢጠራም ሳይመጣ የቀረ ሲሆን፣ ፕሬዝዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ ግን በስነ ስርዓቱ ላይ ተገኝተዋል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በዚሁ የሽልማት ስነ ስርዓት ላይ አባ ገ/መድህን በወርቅ የተሰራ ሜዳሊያ እና ዋንጫ፣ ፕሬዝዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ የግድግዳ ሰዓት ለመለስ ዜናዊ ደግሞ የወርቅ ሰዓት እንደተሸለሙ ታውቋል:: በዕለቱ አቶ መለስ በስፍራው ያልተገኙ በመሆኑ «አቡነ ጳውሎስ ጳጳሶችን አስከትለው ቤተ መንግስት ሄደው እንዲሸልሙልን» በማለት መሉጌታ አስራተ ካሣ መግለጫ የሰጠ ከመሆኑም ባሻገር በተለይም በዚህ ስነ ስርዓት ላይ ደጋግሞ «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት እንዲስፋፋ ያደረገው የኢህአዴግ መንግስት ነው» በማለት ሲገልፅ ፕሬዝዳንት ግርማ ተናድደው ማይኩን ተቀብለው «አንዳንዴ እውነት መናገር ጥሩ ነው:: አሁን ሙሉጌታ የተናገረው ስህተት ነው የኦርቶዶክስ እምነትን ያስፋፋው የኢህአዴግ መንግስት ሳይሆን የንጉሱ መንግስት ነው:: ይህንን መካድ የለብንም» በማለት ሙሉጌታ አስራተ ካሣን አሳፍረውታል:: ከሽልማት አሰጣጡ ከጥቂት ቀናት አስቀድሞ የተሰበሰበው ገንዘብ መጠኑ ይታወቅ አስረዱን ተብለው ሙሉጌታ አስራተ ካሣንና ወ/ሮ እጅጋየሁ በየነ ቢጠየቁም አሻፈረኝ በማለት ያሰቡትን ጥቂት ሽልማቶች ገዝተው ያከናወኑ ሲሆን፣ የተቀረው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ ያልታወቀ መሆኑ ታውቋል::

የአፍሪካ ሕብረት 10ኛ የመሪዎች ስብሰባ ከጥር 22 ቀን እስከ ጥር 24 ቀን 2000 ዓ.ም በአዲስ አበባ በተካሄደበት ወቅት የሻዕቢያ ቅጥረኞች በመሪዎቹ ላይ አደጋ ሊጥሉ ነው በሚል አዲስ የማስደንገጫ ድራማ ለመስራት ከደህንነትና ከፖሊስ ከፍተኛ የሕወሓት ባለሥልጣናት የተውጣጣ አንድ ቡድን ሥራውን ሲያከናውን ሰንብቶ ያልተሳካለት በመሆኑ ድራማውም መክሸፉን ለደህንነት ቢሮ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ገልፀዋል::

ምንጮቹ አክለውም እነዚህ የወያኔ የደህንነት እና የፖሊስ ባለሥልጣናት የተካተቱበት ኮማንድ ፖስት የተሰኘው ቡድን ምንም እንኳዋን የሰሩት ድራማ የከሸፈባቸው ቢሆንም ሌላ ድራማ አዘጋጅተው በአዲስ መልክ አዲስ ስልት ነድፈው እየተንቀሳቀሱ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል::

ባለፈው ሳምንት ይህንኑ በዜና ዘገባችን ላይ የገለፅን ሲሆን አሁን ደግሞ ከጥር 25 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ኮማንድ ፖስት የተባለው ይኸው የወያኔ ከፍተኛ የደህንነትና የፖሊስ ባለሥልጣናት ያሉበት ቡድን በስራቸው ዙሪያ ያጋጠማቸውን ችግርና የወሰዱት እርምጃ ምን እንደነበረና ቀጣይ ሊወስዱ የተዘጋጁበት እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል እየተወያዩና እያሴሩ መሆኑን እነዚሁ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ገልፀው በተለይም ባለፉት የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ወቅት አንዳችም ችግር ሳያጋጥም በመጠናቀቁ እርስ በእርስ ሲሞከሻሹ እንደነበርም አስረድተዋል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሌላው በዚሁ የፖሊስና የደህንነት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ስብሰባ ላይ የተነሳው አጀንዳ ከዚህ ቀደም ከከተማዋ አዲስ አበባ እና ትልልቅ ከተሞች የጉዳና ተዳዳሪዎችና ሴተኛ አዳሪዎችን ያለ ቅድመ ዝግጅት አፍሰዋቸው በድብቅ ስፍራ አስቀምጠዋቸው ያለ ሲሆን በተጨማሪም በቅርቡ አፈሳ ለማካሄድ የታቀደ ሲሆን ታፍሰው የተወሰዱትን ዜጐች በነፃ መልቀቅ ለዚህ መንግስት ስጋት በመሆናቸው አንድ የፈጠራ ክስ ተመስርቶባቸው ወደ ዘብጥያ ለማውረድ እያሴሩ መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

የወያኔ መንግስት እራሱ በፈጠረው እና ሆን ብሎ እንዲሆን ባቀደው መሠረት የሀገሪቷ ዜጐች የሚበሉት አጥተው ለጉዳና ተዳዳሪነትና ለሴተኛ አዳሪነት የተዳረጉ መሆኑ እየታወቀ ከነችግራቸው እንኳዋን እንዳይኖሩ እያፈሰ እንደ ወንጀለኛ ክስ መስርቶ ዘብጥያ ሊያስገባቸው በደህንነትና በፖሊስ ከፍተኛ የሕወሓት ሰዎች ዱለታ መካሄዱ በጣም አሳፋሪና አሳዛኝ ከመሆኑም ባሻገር ሰብአዊነት የጐደለው አረመኔነት ነው ሲሉ ሁኔታውን የተከታተሉ አንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ሲገልፁ ተደምጠዋል::

ዛሬ ከኤርትራ ሸሽተው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ኤርትራውያን በነፃነት በደብረማርቆስና በአዲስ አበባ እንዲኖሩ ተፈቅዶላቸው የኢትዮጵያ ንፁህን ዜጐች ስርዓቱ ባመጣው ችግር እና በፈጠረው ሰንካላ መዋቅር የተነሳ የሚበሉትና የሚቀምሱት ሲያጡ ለጉዳና ተዳዳሪነትና ለሴተኛ አዳሪነት በመዳረጋቸው ብቻ ከየከተማው ታፍሰው የፈጠራ ክስ ተመስርቶባቸው ለእስር እንዲደረጉ መዶለቱ አስገራሚና ሰዎቹ ምን እየሰሩ እንዳሉ እንኳዋን የማያውቁ የአስተሳሰብ ድውዮች ናቸው ሲሉ እነዚሁ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በንዴት ሲገልፁ ተደምጠዋል::

ዛሬ የወያኔው ቡድን በደህንነትና በፖሊስ የሕወሓት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ሀገሪቷና ህዝቦቿ እንደብራና ተወጥረው ባሉበት በዚህ ወቅት በቡሀ ላይ ቆርቆሮ እንዲሉ የጉዳና ተዳዳሪዎችና ሌሎች ስራ አጥ ዜጐችን ማቋቋም ሲገባቸው እንደ ስደተኛ ዜጋ እያፈሱ ወደ ካምፕ መውሰዳቸው በጣም የሚያሳዝን ሲሆን ስደተኞች ናቸው የተባሉትን የኤርትራ ዜጐች ደግሞ እንደልባቸው በከተሞች እንዲኖሩና በየወሩ ተቆራጭ እንዲሰጣቸው መደረጉ ርካሽ ለሆነ ፖለቲካው መጠቀሚያ እንደሆነ የገለፁት አንድ የፖሊስ መኮንን ይህንን ድርጊት ለመፈፀም እየተወያዩ ያሉት ሰዎች በሙሉ አውቃቸዋለሁ በመሆኑም ህሊና የሌላቸው የአስተሳሰብ ደሀዎች ደደቢት አመጣሾች በመሆናቸው ድርጊቱን አይፈፅሙም ብዬ አልከራከርም ሲሉ ያላቸውን አስተያየት ለተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ገልፀዋል::

ዜጐች በደህነታቸው ብቻ አይናችሁን ለአፈር እየተባሉ በወያኔዎች እየታፈሱ በሚወሰዱበት በዚህ ወቅት ሰሞኑን የተቃዋሚ አባሎች ናቸው የተባሉ 5



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ያህል ወጣቶች በወያኔ ወታደሮች ተይዘው ወደ አዲስ አበባ መምጣታቸውን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

ከምዕራብ ኢትዮጵያ ከጅማ ዞን ውስጥ የኦነግ ታጣቂ ናቸው የተባሉ 5 ወጣቶችን እጅና እግራቸውን አስረው መትረየስ በተጠመደባት ታርጋ ቁጥር መከላከያ 01022 ግራጫ መልክ ያላት ቶዮታ ፒክ አፕ መኪና ጭነው በአራት ወታደሮች ታጅበው ወደ መከላከያ የቀድሞው አራተኛ ክፍለ ጦር መሿለኪያ ወደሚገኘው ግቢ ይዘዋቸው መግባታቸውን ምንጮች ገልፀው በሀሰተኛ መንገድ ሰሞኑን በወያኔ መከላከያ በኩል የተሰራው የወያኔ ፊልም ስላለ ለዚህ ድራማ ማድመቂያ ሊያደርጓቸው ሳይሆን እንዳልቀረ ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል::

የወያኔ ወታደሮች ማክሰኞ ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ 5 ቱን ወጣቶች እግር እና እጃቸውን በገመድ አስረው ይዘዋቸው የመጡ ሲሆን አብረዋቸው አንድ የኮኖኔል ማዕረግ ያለው የወያኔ ከፍተኛ መኮንን በሹፌር በመሆን የታርጋ ቁጥር መከላከያ 03398 ቶዮታ ላንድ ክሩዘር ከወገብ በላይ ሲልቨር ቅብ ከወገብ በታች ቀይ ቀለም በተቀባች መኪና የመጣ መሆኑንም እነዚሁ የመከለከያ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል::

የወያኔው የመከላከያ ሚኒስቴር ሰሞኑን አዲስ «የተቆረጡ እጆች» በሚል በኦጋዴን ግንባር የተካሄደውን ውጊያ ለሕዝብ ይፋ አደረገ::

ረቡዕ ጥር 28 ቀን ምሽት በ2:30 ላይ ያሳየው ይኸው የቅንብር ፊልም የወያኔ ወታደሮች የማይሞቱ ብረት ለባሽ ሆነው የታዩበትና በርካታ ጉዳት ሲያደርሱ በ1995 ዓ.ም በኦጋዴን ውስጥ የአልቃይዳ አባሎችን ገደልን ብለው ያሳዩትን ፊልም ሞንታጅ አያይዘው ያቀረቡ ሲሆን፣ ፊልሙ ምንም አይነት ተዓማኒነት የሌለው ፍፁም ውሸት መሆኑን የፊልም ባለሙያዎች በግልፅ ሲተቹ ተደምጠዋል::

ትክክለኛ የውጊያውን ቅጅ ሁለት የውጭ ሐገር ዜጎች በድብቅ ሆነው ሲቀርፁና እና ለአለም ሕዝብ ይፋ ሊያደርጉ የነበረ ቢሆንም የወያኔ ከፍተኛ መኮንኖች ስለደረሱባቸው ፊልሙን ቀምተው ለጥቂት ቀናት አስረዋቸው ከሀገር ያባረሯቸው መሆኑ አይዘነጋም::

አሁን ወያኔ ለህዝቡ አሳየሁት ያለው ፊልም የውጊያውን ገፅታ ፍፁም የማያሳይ የራሱን ገመና ያጋለጠ መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

የወያኔ ቡድን ለስርዓቱ እድሜ ማራዘሚያ ይሆነኛል በሚል ከየገጠሩ በተለይም ደግሞ ከትግራይ በብዛት መልምሎ በሁርሶ እና በጦላይ የጦር ካምፕ አሰልጥኖ ያስመረቃቸው ፖሊሶች በአዲስ አበባ ከ4ሺህ በላይ የሆኑትን የመደበ ሲሆን



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እነዚሁ ፖሊሶች ከአዲስ አበባ ወጣቶች ጋር መግባባት ተስኗቸው በቀየኑ እየተደባደቡ እንደሚገኝ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሱን ዘገባዎች ገለፁ።

በተለይም በልደታና በኮልፌ ቀራኒዮ እንዲሁም ቃሊቲ አካባቢ ካሉ ወጣቶች ጋር መግባባት ባለመቻላቸው በየቀኑ 8 ፖሊሶችና ከዚያም በላይ በመሆን ወጣቶቹን ሲደበድቡ ወጣቶቹ ደግሞ ጨለማን ተገን በማድረግ በፖሊሶች ላይ ጥቃት እየሰነዘሩ ለከፍተኛ ጉዳት እየዳደረጓቸው መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆ ወጣቱ በተወለደበት ሰፈር መዋልና ማምሸት ተከልክሎ እንደ አፓርታይድ ዘመን በየሜዳው ተቀጥቅጦ እየተጣለ መሆኑን እና ሕዝቡም በምሬት «ልጆቻችን ወዴት ይሂዱላችሁ?» እያሉ እየገለፁ መገኘታቸውንም ጨምሮ ያስረዳል።

ወያኔ በዘረጋው ሰንካላና ትውልድ ገዳይ በሆነ የትምህርት ፖሊስ ምክንያት በርካታ ወጣቶች የ10ኛ ክፍልን ጨርሰው ያለ አንዳች ስራ እንዲቀመጡ ተደርጉ እየተጫወተባቸው ከመገኘቱም በላይ በተወለዱበትና ባደጉበት ሰፈር ለምን አየናችሁ እያሉ ከትግራይ በመጡ አዲስ ምልምል ፖሊሶች እየተደበደቡ መገኘቱ የአዲስ አበባ ወጣቶች በንዴትና በብስጭት በፖሊሶች ላይ አፀፋ እርምጃ እየወሰዱ እንዳሉም ዘገባው አብራርቷል።

በሌላ በኩል የወያኔው ዘራፊ ቡድን በ1989 ዓ.ም የለገደንቢ ወርቅን ለሼህ መሐመድ አላሙዲን በ1 ቢለዮን 700 ሚለዮን ብር ሸጦ ገንዘቡን ባለሥልጣናቱ የት እንዳደረሱት እንዳልታወቀ የደረሰን ዘገባ አጋለጠ።

ሼህ መሐመድ አላሙዲን በ1989 ዓ.ም የለገደንቢ የወርቅ ማዕድንን ገዝተው ስራ የጀመሩ ሲሆን ከዚያን ወቅት ጀምረው ለሀገሪቱ አንዳችም አይነት ግብር ሳይከፍሉ መቅረታቸውን የደረሰን ዘገባ ገልጿል። በየዓመቱ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር የሚዝቀው ይኸው የወርቅ ማዕድን አንዳችም ገቢ ለሀገሪቱ ሳይሰጥ የቆየ አንዳችም ጥያቄ ያልተነሳበት ሲሆን በአንፃሩ ግን ከ5ሺህ ብር በታች በሆነ ካፒታል የሚንቀሳቀሱ ኢትዮጵያውያንን «ደንብ ተላልፋችኋል» እየተባሉ ሱቆቻቸው ታሽጉባቸው ቤተሰቦቻቸውን እየበተኑ እንደሚገኙ ዘገባው ጨምሮ አስረድቷል።

ወያኔ በ1989 ዓ.ም 1.7 ቢሊዮን ብር ከሼሁ ላይ ወስዶ ገንዘቡን የት እንዳደረሰ ያልታወቀ ሲሆን በተለይም በአንድ ወቅት በአለም ባንክ ውስጥ አስቀምጠዋል ተብሎ ስም ዝርዝራቸው የወጣው የባለሥልጣናቱ ስም ይህንኑ እና ሌላም ገንዘቦች ተከፋፍለው ሳይሆን አይቀርም በማለት አንዳንድ ሰዎች ግምታቸውን ይሰነዝራሉ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com